# Amharic A: literature – Standard level – Paper 2
# Amharique A : littérature – Niveau moyen – Épreuve 2
# Amhárico A: literatura – Nivel medio – Prueba 2

Thursday 5 May 2016 (afternoon)
Jeudi 5 mai 2016 (après-midi)
Jueves 5 de mayo de 2016 (tarde)

1 hour 30 minutes / 1 heure 30 minutes / 1 hora 30 minutos

---

### Instructions to candidates

- Do not open this examination paper until instructed to do so.
- Answer one essay question only. You must base your answer on at least two of the part 3 works you have studied and compare and contrast these works in response to the question. Answers which are not based on a discussion of at least two part 3 works will not score high marks.
- You are not permitted to bring copies of the works you have studied into the examination room.
- The maximum mark for this examination paper is **[25 marks]**.

### Instructions destinées aux candidats

- N’ouvrez pas cette épreuve avant d’y être autorisé(e).
- Traitez un seul sujet de composition. En basant votre réponse sur au moins deux des œuvres de la troisième partie que vous avez étudiées, vous devez comparer et opposer ces œuvres dans le cadre du sujet. Les réponses qui ne sont pas basées sur au moins deux des œuvres de la troisième partie n’obtiendront pas une note élevée.
- Vous n’êtes pas autorisé(e) à apporter des exemplaires des œuvres que vous avez étudiées dans la salle d’examen.
- Le nombre maximum de points pour cette épreuve d’examen est de **[25 points]**.

### Instrucciones para los alumnos

- No abra esta prueba hasta que se lo autoricen.
- Conteste una sola pregunta de redacción. Base su respuesta en al menos dos de las obras estudiadas de la parte 3, comparándolas y contrastándolas en relación con la pregunta. Las respuestas que no se basen en al menos dos obras de la parte 3 no recibirán una puntuación alta.
- No está permitido traer copias de las obras estudiadas a la sala de examen.
- La puntuación máxima para esta prueba de examen es **[25 puntos]**.



2216 – 0012

© International Baccalaureate Organization 2016

ከሚከተሉት **አንዱን** ጥያቄ መልስ(ሽ)። መልሱ በክፍል 3 ባጠናሀቸው (ባጠናሻቸው) **ቢያንስ ሁለት** ስራዎች ላይ መመስረት አለበት። ስራዎቹን **በማወዳደርና በማነጻፀር** ጥያቄውን መልስ(ሽ)። በክፍል 3 ባጠናሀቸው (ባጠናሻቸው) ቢያንስ ሁለት ስራዎች ላይ **ያልተመሰረተ** መልስ ከፍተኛ ነጥብ **አያስገኝም**።

**ድራማ/ተውኔት**

1. ባጠናሃቸው ቢያንስ ሁለት ስራዎች ውስጥ ፀሀፊ ተውኔቶቹ በድራማዎቻቸው እንዴት ተመልካቾቻቸው ገፀባህርያቶቻቸውን በሚገባ እንዲረዱላቸው እንዳደረጉ አስረዳ።

2. ስራቸውን ያጠናህላቸው ሁለት ፀሀፊ ተውኔቶች እንደምን የስራዎቻቸውን ታሪኮች ለመድረክ ትወና እንዳቀረቡ አስረዳ። የትኞቹ ተውኔቶች የተሳኩ እንደሆኑና ስኬቱም ለምን እንደተገኘ ግለጽ።

3. በትራጀዲና በኮመዲ መካከል ያለው መሰረታዊ ልዩነት የሰውን ተፈጥሮ የሚያቀርቡበት መንገድ ነው። ባጠናሃቸው ሁለት ተውኔቶች ውስጥ የሰው ተፈጥሮ የቀረበበትን መንገድ በንጽጽር በማሳየት የሀሳቡን ትክክለኛነት አስረዳ።

**ረጅም ልቦለድ**

4. ያነበብካቸውን ቢያንስ ሁለት ስራዎች በማነፃፀር ደራስያኑ መቼትን በመጠቀም እንዴት ገፀባህርያቶቻቸውን በአግባቡ እንደሳልዋቸው አሳይ።

5. አንባብያን ከታሪኩ ጋር ራሳቸውን ሲያዛምዱ የልቦለዱ ታሪክ አስደሳች ይሆንላቸዋል። ባጠናሃቸው ቢያንስ ሁለት ስራዎች ውስጥ ደራስያኑ አንባቢዎቻቸው ከልቦለዶቹ ታሪኮች ጋር እራሳቸውን እንዲያዛምዱ ያደረጉበትን መንገድ አስረዳ።

6. ረጅም ልቦለድ መነበብ እንዲችል በመጨረሻ አንድ ነገር መከሰት ይገባዋል። ባጠናሃቸው ቢያንስ ሁለት ስራዎች ውስጥ ደራስያኑ የልቦለዶቻቸውን መጨረሻ እንዴት እንደተጠቀሙበት አብራራ።

**ስነ ግጥም**

7. ስራቸውን ያነበብክላቸው ቢያንስ ሁለት ገጣምያን ምፀትን እንዴት እንደተጠቀሙበትና ያስገኘላቸውን ጥቅም አስረዳ።

8. ስራቸውን ያነበብክላቸው ሁለት ገጣምያን የቃላት ምርጫን በመጠቀም ስራዎቻቸውን እንዴት እንዳቀረቡ አብራራ።

9. ተምሳሌት በሁለት መንገድ ይሰራል። እራሱ አንድ ነገር ነው፤ ከዚህ ሌላ ተጨማሪ ጥልቅ ነገር ይጠቁማል። ስራቸውን ያነበብክላቸው ቢያንስ ሁለት ገጣምያን በስራዎቻቸው ተምሳሌትን አንድን ነገርና በተጨማሪም ጥልቅ ነገርን ለመግለጽ እንዴት እንደተጠቀሙበት አስረዳ።

## አጭር ልቦለድ

**10.** ግጭት የአጭር ልቦለድ ታሪክ ወደፊት እንዲራመድ ያደርጋል:: ባነበብካቸው ቢያንስ ሁለት ስራዎች ውስጥ ደራሲዎቹ በግጭት አማካኝነት ታሪኮቻቸውን እንዴት እንዳሳደጉ አብራራ::

**11.** ትልም ልብ ሰቀላን በመፍጠር ታሪኩ ጡዘት እስኪደርስ ድረስ አጉዋጊ ሆኖ እንዲቀጥል ማድረግ አለበት:::: ባጠናሃቸው ቢያንስ ሁለት ስራዎች ውስጥ ደራስያኑ ልብ ሰቀላን በመጠቀም ታሪኩ ጡዘት ላይ እስኪደርስ ድረስ አጉዋጊ ሆኖ እንዲቀጥል እንዴት እንዳደረጉ አሳይ::

**12.** ገፀባህርያት አንባቢው ከአጭር ልቦለዶቹ ጋር እራሱን እንዲያዛምድ የሚያደርግባቸው የደራሲው ዋና መሳርያዎች ናቸው:: ባጠናሃቸው ቢያንስ ሁለት ስራዎች ምሳሌነት የሀሳቡን ትክክለኛነት አስረዳ::